# የአርበኞች ግንቦት 7 ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሊያደርግ የነበረው ህዝባዊ ስብሰባ ሳይካሄድ ቀረ

ፓርቲው በዛሬው ዕለት በባህዳር ከተማ በክልሉ ምክር ቤት ሊያካሄድ አስቦ የነበረው ህዝባዊ ውይይት በተፈጠረ አለመግባባት ሳይካሄድ ቀርቷል።

ውይይቱ ሳይካሄደ የቀረው አርበኞች ግንቦት 7 የአማራን ህዝብ አይወክልም በሚል ከወጣቶች ጋር በተፈጠረ አለመግባባት መሆኑ ታውቋል፡፡

ወጣቶቹ ውይይቱ በተጠራበት አዳራሽ አካባቢ ተቃውሟቸውንም አሰምተዋል፡፡

ወጣቶቹ ስብሰባው ህዝባዊ በመሆኑ ወደ አዳራሽ በመግባት ስብሰባውን እንካፈላለን በማለት በር ላይ ከነበሩት የጸጥታ አካላት ጋር መጋጨታቸውም ተገልጿል።

የዝግጅቱ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ሃይለ እየሱስ ጌትነት እንደተናገሩት ስብሰባው እንዳይካሄድ ያረጉት ማንነታቸው ያልታወቁ ወጣቶች አዳራሽ ውስጥ በመግባት የነበሩ ባነሮችን በማውረድ የራሳቸውን ባነር ሰቅለዋል፡፡

በባህርዳር ከተማ ከግጭቱ ጋር በተያያዘ የተኩስ ድምጽ እንደነበር፤ ነገር ግን የተጎዳ ሰው እንደሌለ ተገልጿል፡፡

ሪፖርተር፡- ስመኘው ይርዳው





